# የምላስ ተኩስ በዝቶ

ሀማ ቱማ

ላስቲክ ቤት ሆኖልን ሩዝም እንጀራ
ኢትዮጵያን አስባላን ሞተን ሞት ስንፈራ፡፡

ወንዶቹም አለፉ ግፍን እየገፉ
ሴቶችም እንዲሁ ወንዱን እያስናቁ
በራቁት ሰውነት እነ አጅሬ ቀሩ
ውርደት የለበሱ ጨቋኝን ያቀፉ፡፡

ሌባ ጣት ቀስረው ባሰት የከሰሱ
ለሀቅ የቆሙትን በውሸት ያጠቁ
ሌሊቱ ሲነጋ ሁሉም ተጋለጡ
ባባዕድ መዲናም አልቻሉም ሊጠፉ
የሀሳዊ መሲህ ታሪክ ሁሌ ክፉ፡፡

ትኋን መዥገር ወዶ ርቃኑን ሚተኛ
ውርደት ሞትን ወዳጅ የባዕድ ቅጥረኛ
ሀገሩን የሸጠ ሸክም ወዳድ ጌኛ
ለነጭ ይፀልያል ሲነሳ ሲተኛ፡፡

ረሃብን የረሳ ጥሜት የዘነጋ
ቅማልን የረሳ ትኋንን የረሳ
ሥቃይን የረሳ ሞትን በሩቅ ያለ
ባዕድ ሀገር ሆኖ ፋኖውን ወቀሰ
ቶሎ ቶሎ ሙቱ ላገር አብቁኝ አለ ፡፡

እንደ ዘመናይ እብድ ግራ ቀኙን ሰድቦ
ላያበላ ጋብዞ ላይገድል ፎክሮ
በቃኝ ከፋኝ ይላል አሜሪካ ገብቶ
በአፍ ተኩሶ ገዳይ የዘንድሮ ፋኖ
ባለ አንቀልባ ትግል በሀገር ሁሉ ሰፍኖ
ስለ ትግል ማውሳት ትግልን ተክቶ፡፡